# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

# የ2017 በጀት ዓመት የስድስት ወራት
# የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

የታህሣሥ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

| ማውጫ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | ርዕስ | |
| 1 | መግቢያ | 2 |
| 2 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ | 2 |
| 3 | በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና | 3 |
| 4 | የዓበይት ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎን | 12 |
| 5 | ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች | 12 |
| 6 | በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ተግባራት | 13 |
| 7 | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የሰው ኃይል መግለጫ | 14 |
| 8 | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የፋይናንስ አፈጻጸም | 15 |
| 9 | ማጠቃለያ | 16 |
| 10 | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት ሪፖርት እና የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም | 18 |

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና የ3 ዓመት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ (2016-2018) መሰረት በማድረግ በ2016 በጀት ዓመት ያልተጠናቀቁ ተግባራትን በማካተት የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ተገምግሞ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2017 በጀት ዓመት በ6 ወራት የተከናወኑ የዋና ዋና የተግባራት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2017 በጀት ዓመት በ6 ወራት ውስጥ የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማለትም መግቢያ፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች፣ በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት እቅድ አፈጻጸም ትንተና እንዲሁም በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የተወሰዱ መፍትሄ እርምጃዎች እና ማጠቃለያ በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ

መንግስት በከፍተኛ በጀት ከሚያስገነባቸው የመሰረተ ልማት አውታሮች አንደኛው የጥራት መሰረተ ልማት ተቋም ግንባታ አንዱ በመሆኑ እና የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ላቦራቶሮችና ዎርክሾፖች በፋሲሊት ለማደራጀት በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር በኩል ሲከናወን የነበረው የላብራቶሪዎች፣ ለወርክሾፖች እና ለቢሮዎች ግልጋሎት የሚሰጡ ስድስት ከ4- እስከ 5 ወለል ያላቸው የህንፃ ግንባታ ተጠናቆ ተመርቋል፡፡ በተጨማሪም በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት በአለም ባንክ ብድር የተለያዩ መሳሪያዎች የተገዙ በመሆናቸው የሥነ-ልክ ተቋምን አቅም በማሳደግ ለአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ስኬት ከምርታማነት ጥራትና ተወዳደሪነት አንፃር ኢንስቲትዩቱ አይነተኛ ሚናውን እንዲጫወት ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል የኢንስቲትዩቱ አዲሱ የማቋቋሚያ ደንብ ጸድቆ ስራ ላይ የዋለ በመሆኑ በዘርፉ የሃገሪቱ ፍላጎት አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ጋር ለማጣጣም እና ለሃገራዊ ልማት የሚያበረክተውን ሚና በብቃት ለመወጣት በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የተደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በመከተል በዘርፉ የጥናትና የምርምር ተግባራት፣ የካሊብሬሽን፣ የቴክኒክ አገልግሎቶች፣ የስልጠና እና የማማከር ስራዎችን ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ እንዲሁም በማቋቋሚያ ደንብ የተሰጠውን ኃላፊነት እና ተግባር በአግባቡ ለመወጣትና በቀጣይ የታቀዱትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት አጥንቶ በማጸደቅ ምደባ ተከናውኖ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ የሰው ኃይል ግንባታን በተመለከተ በ2017 በጀት ዓመት

ለ135 ሠራኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለአንድ ወንድ ሠራተኛ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል፡፡

የሀብት አጠቃቀም በተመለከተ በኢንስቲትዩቱ በውስጥ ኦዲት የክትትል ስራዎች የሚሰሩ ሲሆን የ2016 በጀት ዓመት የፊሰስ ሂሳብ ሪፖርት እና የ4ኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡ ከለውጥና መልካም አስተዳደር አንጻር ለተገልጋዮች የቅሬታ እና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርአት የተዘረጋ በመሆኑ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በየደረጃው የመፍታት ስራ ተሰርቷል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ አገልግሎታችንን ለደንበኞች ምቹ እና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር በአዲሱ ህንጻ ላይ የደንበኞች አገልግሎቱን ምቹ ለማድረግ የተሰራ ሲሆን በአለም ባንክ ብድር በጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ድጋፍ አዳዲስ የኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ለማድረግ የካሊብሬሽን አገልግሎት፣ የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና አገልግሎትን በክፊል እና የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት በኦንላይን ለደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ጠት እንድንዲችል እየተሰራ ይገኛል፡፡

### 3. በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና

አጠቃላይ የኢንስቲትዩቱ የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም **84.5%** ሲሆን በዝርዝር ሲታይ የተገልጋይ ዕይታ አፈጻጸም 85.5%፣ የፋይናንስ ዕይታ 91.3%፣ የውስጥ አሰራር ዕይታ 73.5% እና የመማማርና ዕድገት እይታ 91.5% ነው፡፡

**ግብ 1፡ የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ (ክንዉን 86%)**

**1.2. የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 79.2%)**

1.2.1. ለ17000 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ በመካኒካል ሥነ ልክ 7971፣ በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ሙቀት ሥነ ልክ በሙቀት 4199፣ በኤሌክትሪካል 281 እና በቅርንጫፍ ላብራቶሪ 1023 በድምሩ 13474 የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል **(ክንውን 79.2%)**፡፡

**1.3. የጥገና አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን** 79.4%)

1.3.1. ለ155 ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ48 የህክምና የሳይንስ መሳሪያዎች እና ለ87 ከህክምና መሣሪያዎች ውጭ በድምሩ ለ135 መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ተሰጥቷል (ክንውን 79.4%)፡፡

**1.4 የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 100%)፡፡

1.4.1 በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች ስልጠናዎችን ለመስጠት ታቅዶ፡-

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

- ከአሜሪካው ፋርማኮፒያ ጋር በመተባበር
  - ✓ ከተለያዩ ክልሎች ለተመረጡ ለ 50 (ሴ=20, ወ=30) የባዮሜዲካል መሐንዲሶች በCold chain equipment and General Metrology ላይ በሃዋሳ ከተማ ለ3 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ✓ ለ 8 (ሴ=1, ወ=7) የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች በርስበርስ ንጽጽር ፕሮግራሞች ላይ በአዳማ ከተማ ለ2 ቀናት የጽንሰ ሀሳብ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከሸገር ከተማ አስተዳደር ከ12ቱም ክፍለ ከተሞች ለተወጣጡ 117 (ሴ=57,ወ=60) የንግድ ቢሮ አመራሮችና ቡድን መሪዎች በህጋዊ ስነልክ አሰራር ላየሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ለ23 (ወ =9 ሴ= 14) የአዲስ አበባ ተግባረእድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ተማሪዎች በ ይዘት, ግዝፈት, ሚዛን, ዳይሜንሽናል እና ግፊት አለካክ መስኮች የህጋዊ ስነልክ አሰራር ላይ የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ**

- ➢ ከጤና ጥበቃ ጋር በመተባበር ለ28 ባዮሜዲካል መሃንዲሶች በአንድ ዙር ሥልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 133%)፡፡

1.5 **የቴክኒክ ድጋፍ እና ምክር አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 100%)፡፡

1.5.1 ሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለግል ባለሃብት፣ ለህጋዊ ሥነ-ልክ፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለሚያቋቁሙ የግል ባለሃብት ወ.ዘ.ተ ጥያቄ ለሚያቀርቡ 100% የቴክኒክ እና የምክር  አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ፡-

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

- ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ቀደም ሲል በተዘጋጀላቸው የመለኪያ መሳሪያዎች ግዢ ዝርዝር መስፈርት /Specification/ መሰረት ስለመቅረባቸው የኢንስፔክሽን ስራ ተሠርቷል፡፡
- ለኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን  የውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም  ጥያቄ አቅርበው
  - ✓ የመግቢያ መረጃ ተጠናክሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡

- ✓ የማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ግዢ መፈጸም የሚያስችል በ volume, mass, balance, force and pressure ቴክኒካል እስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቷል፡፡
- ✓ በቀጣይነትም የጥራት ሰነድ ዝግጅትና የቴክኒክ ድጋፍ በሚጠይቁ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ**

- ➢ የጥገና ወርክሾፐ ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት 100% የቴክኒክ እገዛ ለማድረግ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለሚቀርቡ የምክር ጥያቄዎች የምክር አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ ከጤና ጥበቃ ጋር በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተዘጋጁ፡-
    1. medical device roadmap
    2. guideline for medical device maintenance
    3. Medical device management strategy ዶክመንቶች ላይ 4 መሀንዲሶች በማሳተፍ እገዛ አድርገናል፡፡

1.6 **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 0%)፡፡

1.6.1 ለ100 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ አልተከናወነም (ክንውን 0%)፡፡ ያልተከናወነበት ምክንያት በአዲሱ የፀደቀው ደንብ ላይ ባለመኖሩ ን/ቀ/ት/ሚ ተጠይቆ ባለሀብቶችን ለማበረታታት ብት ማረጋገጫ እንደማይጠየቅ በመገለጹ ነው፡፡

**ግብ 2፡ ተደራሽነትን ማሳደግ (ክንውን 82.7%)**

**.2 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለኅብኚዎች ሳቢና ኢንተራክቲቭ እንዲሆን ማድረግ (ክንውን 100%)**

2.2.1 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት የኢንስቲትዩቱን ድህረ ገጽ 24/7 ደህንነቱን ለመጠበቅ እና ለደንበኞች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ፡-

1. አየር ላይ ያለው የነባሩን ድረ ገጽ ደህንነት የመጠበቅ እና ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ክትትል የማድረግና የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡
2. የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት አሁናዊ የተቋሙን ሁኔታ ያገናዘበ መረጃ እንዲኖረው መረጃዎች ተከልሰዋል (ክንውን 100%)፡፡

2.2.2 ለድህረ ገጽ ተጠቃሚዎች ድጋፍ እና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ መረጃዎች እና ዜናዎች በድረ ገጹ ላይ እንዲጫኑ ጋፍ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ** (ክንውን 91.36%)፡፡

**3.1 የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት እና የበጀት አጠቃቀም መከታተል** (ክንውን 85.3%)፡፡

3.1.1. የፀደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት 100% ለመጠቀም ታቅዶ መደበኛ በጀት 64.4% መጠቀም ተችሏል፡፡ የካፒታል በጀት የላብራቶሪ መሣሪዎች ግዢ በጨረታ ሂደት ላይ በመሆኑ እና ለላብራቶሪ የሚውል ተሽከርካሪ ግዢ በማስፈቀድ ሂደት ላይ በመሆኑ አልተከናወነም (ክንውን 64.4%)፡፡

**3.2. የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ** (ክንውን 87%)፡፡

3.2.1. 5,700,000 የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ ታቅዶ ከሀምሌ 2016 እስከ ታህሳስ 15 ቀን 2017 ዓ.ም ከካሊብሬሽን አገልግሎት፣ ብር 4,785,794.06 ከሳ.መሳ.ጥገና እልግሎት ገቢ ብር 179,256.09 በአጠቃላይ ብር 4,965,050.15 ገቢ ተሰብስቧል (ክንውኑ 87%)፡፡

**3.3 የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** (ክንውኑ 100%)፡፡

3.3.1 4 የኦዲት ሪፖርት ለማዘጋጀት ታቅዶ የ2016 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት፣ የ4ኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት፣ የ2017 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የስጋት አካባቢ ተለይቶ በንብረት እና በነዳጅ ላይ የክዋኔ ኦዲት እየተሰራ ይገኛል 100%)፡፡

**ግብ 5. አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** (ክንውን 82%)፡፡

**5.1 ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት** (ክንውን 100%)፡፡

**5.1**.2 በውስጥ ካሊብሬሽን፣ በተንቀሳቃሽ እና በመስክ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለማሰራጨት ታቅዶ በውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ በሙቀት እና በኤሌክትሪካል ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ጊዜያቸዉ የደረሰ ማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል (ክንውን 100%)፡፡

5.3. **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት** (ክንውን 58%)፡፡

5.3.1 በሁለት ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች የግዝፈት እና የሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች በኢትዮጵያ የአክሪዲቴሽን አገልግሎት አክሪዲቴሽን ለማግኘት ታቅዶ የነበረዉን እቅድ በዋናዉ መስሪያ ቤት ከDAAKS በተገኘዉ እዉቅና ለማስቀጠል በእንቅስቃሴ ላይ ነው (ክንውን 60%) ፡፡

5.3.2 በቀጣይ ዓለም አቀፍ ዕዉቅና የሚጠየቅባቸው (የጨረራ፣ የፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እና የኬሚካል) የአለካክ መስኮች የልኬት ወሰን ለመለየት ታቅዶ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ የአለካክ መስክ (Calibration of wave Length) ላይ የልኬት ወሰን ተለይቷል (ክንውን

50%)፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት የህንጻ ግንባታ በመዘግየቱ በተለይ የሊድ ዶር ጥገና (Lead Door Maintenance) ምክንያት የጨረር አመንጪ ማሽኖች ተከላና ስልጠና አለመጠናቀቁ የጨረራ አለካክ መስክ ላይ የልኬት ወሰን መለየት ባለመቻሉ ነው፡፡

5.4 **በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB) ማስመዝገብ** (ክንውን 100%)፡፡

5.4.2 በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ ለማስመዝገብ ታቅዶ በይዘት 1 እና በኤሌክትሪክ 3 በድምሩ 4 ላቦራቶሪዎች የመለካት አቅም ማስመዝገብ ተችሏል (ክንውን 100%)፡፡

5.5 **ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ**(ክንውን 100%)፡፡

5.5.1 ከአህጉራዊ AFRIMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ለማመቻቸት ታቅዶ 17ኛው የAFRIMETS GA ስብሰባ ከሐምሌ 22 - 26 ቀን 2016 ዓ.ም በሙቀት በonline እና በኤሌክትሪካል በአካል በመገኘት ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ ተሳትፎ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 6. የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** (ክንውን 75%)፡፡

**6.1. የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ** (ክንውን 75%)፡፡

**6.1.2** በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration, frequency counter and generator' ስልጠናዎችን ማግኘት፣የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማጠናቀቅ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ ቢጋራ (TOR) ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ነገር ግን እስከ አሁን በተለያዩ ምክንያት ስልጠና ባይሰጥም በcentrifuge calibration ላይ በራስ ባለሙያ በማንበብ ስልጠና በመስጠት ሰራ ተጀምሯል (ክንውን 50%)፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በራስ ጥረት ስራ መጀመር ቢቻልም የስልጠና ቢጋራ (TOR) ተዘጋጅቶ ቢቀርብም ስልጠና ባለመገኘቱ ነው፡፡

6.1.5 በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ በፎቶሜትሪ /photometer/ የአለካክ መስክ ላይ በኢንስቲትዩቱ አማካሪ በዶ/ር ፍራንዝ አማካኝነት ስልጠና በመዉሰድ የካሊብሬሽን አገልግሎት ተጀምሯል (ክንውን 100 )፡፡

**ግብ 7. የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል (ክንውን 71%)፡፡**

**7.1. የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 71%)፡፡

**7.1.3** የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን የኦንላይን አገልግሎት ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ህክምና መሳሪያዎች ስራ አስፈጻሚ ጋር በጋራ በመሆን የተሰራውን ፖርታል ተገምግሞ ቀሪ ስራዎች የተጠናቀቁ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ የብቃት ማረጋገጫን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የመጨረሻ ዲፕሎይመንት እና የስራ ላይ ልምምድ ለማድረግ ከስምምነት ተደርሷል (ክንውን 95%)፡፡

**7.2. ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ** (ክንውን 50%)፡፡

**7.2.1** በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ለማስጠበቅ ታቅዶ በመደበኛ ፍርድ ቤት በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በጣልቃገብ፤በይግባኝ እና በአፈጻጸም የቀረቡ ጉዳዮች ክርክር ተደርጎባቸው፤ ሁሉም ውሳኔ አግኝተዋል (ክንውን 100%)፡፡

**7.2.2** ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ለማድረግ ታቅዶ የቀረበ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳይ ባለመኖሩ አልተከናወነም (ክንውን 0%)፡፡

**7.3. የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም (ክንውን 80.91%)**

7.3.1 በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ለማጠናቀቅ ታቅዶ በሀገር ውስጥ ግዥዎች በማዕቀፍ ግዥ የጽዳት ዕቃዎች፣የጽ/መሳሪያዎች ፣የደንብ ልብስ ግዥዎች የተፈፀሙ ሲሆን ሌሎች በeGP ሲስተም የተከናወኑ የጥበቃና ጽዳት፣ የኮምፒውተር ጥገና አሸናፊ ድርጅቶች ተለይተዋል፡፡ ሌሎች የዕቃ ግዥዎች ጨረታ አየር ላይ ውሎ በክትትል ላይ ነው (ክንውን 65%)፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በeGP ሲስተም በአግባቡ ስለማይሰራ በግዥ አፈፃፀሙ ላይ ችግር በመፍጠሩ ነው፡፡

**7.4 የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ** (ክንውን 95%)

**7.4.1** በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ለማድረግ ታቅዶ የ2016 በጀት ዓመት ቆጠራ ተጠናቋል፡፡ በተጨማሪም በርካታ ንብረቶች ተለይተውና ተደራጅተው ዋጋቸው ተገምተው ለመቄዶንያ በጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡ በቀጣይ ሁለተኛ ዙር ለማስወገድ እንዲቻል ንብረቶች ተለይተው፣ ተደራጅተውና የዋጋ ግምት ተጠናቆ ለአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲቀርቡ ተደርጓል (ክንውን 95%)፡፡

**ግብ 8. ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** (ክንውን 50%)።

**8.2 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 0 %)።

8.2.1. ከጀርመን (PTB) እና ከደቡብ ኮርያ (KRISS) ሥነ-ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነቶችን ማደስ እና ተግባራዊነቱን ለመከታተል ታቅዶ አልተከናወነም (ክንውን 0%)። ያልተከናወነበት ምክንያት ከፍተኛ አመራሩ ለሕንጻ ምረቃ የዘመቻ ሥራ ላይ በመሆናቸው ነው

**8.3 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 100%)።

**8.3.1** ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት ታቅዶ ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር ከተሰሩ ስራዎች የፎቶሜትሪ እና ራዲዮ ሜትሪ ሥነ-ልክ ዴስክ ከECAE workshop በጋራ መጠቀም፣ ልምድ መለዋወጥ ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም በኬሚካል ሥነ-ልክ ላይ በምን ዙሪያ በጋራ ሊሰራ እንደሚችል ከባለሙያዎች ጋር በጥልቀት በመወያየት አሁን ባለዉ ሁኔታ ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት እና ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ ሊሰራ እንደሚገባ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት የመጣ የደረጃ ፍላጎት ከኬሚካል ሥነ-ልክ ቲ.ሲ ጋር የተገናኘ ዳሰሳ ተሞልቶ ተልኳል በቀጣይም በነዚህ ዙሪያ ሥራዎች የሚቀጥሉ እና ዝርዝር የጋራ መግባቢያ መስፈርቶችም የሚዘጋጁ ይሆናል (ክንውን 100%)።

**ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ** (ክንውን 91%)።

**9.1 የሰው ሀብት ልማት ማልማት** (ክንውን 85%)።

**9.1.2** ለ3 ሰራተኞች ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ለመስጠት ታቅዶ ለ1 ወንድ ሰራተኛ የሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል (ክንውን 33.33%)። አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት የጥራት መንደር ግንባታ ስራዎች ክትትል እና በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት የተገዙ መሳሪያዎች ኢንስታሌሽንና ኮሚሽኒግ ስራዎች በልዩ ትኩረት እና ብቃቱ ባላቸው ባለሙዎችች ክትትል መደረግ ስላለበት በበጀት ዓመቱ የትምህርት እድል ባለመበረታቱ ነው።

**9.2 የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መከታተልና ማጠናከር** (ክንውን 90.8%)።

9.2.1. ማህበራዊ አገልግሎት በተመለከተ ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት 9780 ብር ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 8,856 ብር ድጋፍ ተደርጓል። በተጨማሪም ደመወዛቸው አነስተኛ ለሆኑ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ከሠራተኛ ክበብና ከሌሎች ሠራተኞች በማስተባበር ለአዲስ ዓመት የዱቄትና ዘይት ድጋፍ ተደርጓል። እንዲሁም ለመቅዶንያ አረጋውያን መረጃ 93750 ብር ማዕድ የማጋራት ስራ ተሰርቷል (ክንውን 90.8%)።

9.3 **የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 100%)፡፡

9.3.1 በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የስነምግባር መመሪያ ለማጠናቀቅ፣ ታቅዶ የተቋሙ ሠራተኞች የስነምግባር ደንብ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ለፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተልኳል (ክንውን 100%)፡፡

9.3.2 በተቋሙ በህግ ሀብት ማስመዝገብ የሚገባቸው ሰራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ለመከታተል፣ ታቅዶ አገልግሎት ማቋረጥ 9 (ወ=6 ሴ=3) እድሳት 150 (ወ=89 ሴ=61) አመራሮችና ሠራተኞች ሀብታቸውን አስመዝግበዋል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል (ክንውን 100%)፡፡**

**10.1 የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ (ክንውን 100%)፡**

**10.1.** የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአካባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ለማቅረብ ታቅዶ የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአካባቢው የሚያመነጨውን መጠን በሳምንት አንድ ጊዜ የሰርቪሊያንስ ስራ እየተስራ ይገኛል (ክንውን 100%)፡፡

**10.2 ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት** (ክንውን 100%)፡፡

10.2.1. የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ለማድረግ (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ እና እድሳት) ታቅዶ ፦

- ለ15 ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ተደርጓል፣
- ለአንድ ተሽከርካሪ ኖርማላይዜሽን/በሊትር ተሽከርካሪው የሚጓዘው ኪሎ ሜትር መረጃ በአንበሣ አውቶብስ ድርጅት ተሰርቷል፣
- ለሚወገደው ተሽከርካሪ ዕዳ ዕገዳና የዴክላራሲዮን ኘሮሴስ ከአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ባለሥልጣን ማውጣት ተችሏል፣
- ለ6 ተሽከርካሪዎች ጥገናና ሠርቪስ ተደርጓል፣
- ከገንዘብ ሚ/ር የተሰጠንን የሃይውንዳይ ተሽከርካሪ የዲክላራሲዮን፣ የቦሎ፣ የታርጋና የሊብሬ ኘሮሰስ ተጠናቋል፣
- አዲስ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች የእጅ ማፍታቻ ሥልጠና በአንበሣ አውቶብስ ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፣
- ለግሪን ኤሪያው መከለያ የሰንሰለት አጥር ሥራ ተሰርቷል፣
- ተጨማሪ የፅዳትና የጥበቃ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል፣
- ከኮተቤ ግቢ በርካታ ንብረቶች ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ወደ መገናኛ አዲሱ

ህንፃ እንዲጎገዙ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**10.3 የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ** (ክንውን 100%)፡፡

10.3.1 ለነባር ሲስተሞችን (ኢፍሚስ ፤ ኢጂፒ፤ ኢስሚስ፤ ኢሜል፤ ዌብሳይት) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ

- በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት ለሁሉም የስራ ክፍሎች የጠያቂና አጽዳቂ (role)፣ ፋይናንስ እና መሰረታዊ ስራ አስፋሚ ሥር ላሉ ባለሙያዎች ከፋይናንስ ስራ አስፈጻሚ በቀረበው ጥያቄ መሰረት በድምሩ 95 የኢፍሚስ እና ኢጂፒ አካውንት የማስተካከል ስራ ተሰርቷል፡
- የተጠቃሚዎች የይለፍ ቃላቸውን ለረሱ ባለሙያዎች የአካውንት ሪሴቲን ስራዎች (Account resetting) የ16 የተጠቃሚዎች የይለፍ ቃል ሴቲን (User Password resetting) ድጋፍ ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

**10.3.2** የኢንስቲትዩቱን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ

1. የኢንስቲቲዩቱን የኔትወርክ መሰረተ ልማቶች ደህንነት በየቀኑ የመጠበቅ፤
2. ከኔትወርክ እና ከኢንተርኔት ጋር ተያይዞ ከተጠቃሚዎች የሚቀርቡ የቴክኒክ ድጋፎችን የመስጠት ስራ ተሰርቷል (ክንውን 100%)፡፡

**10.4 የተቋማዊ ለውጥ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት** (ክንውን 100%)፡፡

**10.4.2** የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት እንዲፈቱ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ታቅዶ 5 ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን ከካሊብሬሽን የቀጠሮ መርዘም ፣ የደንበኞች ክፍል የባለሙያ እጥረት መኖሩ እና የቀጠሮ መስጫ ቢሮ ሌላ ህንጻ ላይ መሆኑ ቅሬታ ቀርቦ የሁለቱ ደንበኞች ከጊዜ መረዘም ጋር ተያይዞ የቀረበው እንዲፈታ ተደርጓል፡፡ ቀሪዎቹ በሂደት የሚፈቱ ሆናል፡፡ (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** (ክንውን 100%) ፡፡

**11.1 ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ** (ክንውን 100%) ፡፡

11.1.1 ከመንግስት በጀት የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለመከታተል ታቅዶ

- ለተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ የመኪና ግዥ በተመለከተ ገ/ሚ/ር በደብዳቤ ተጠይቆ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ተመርቶ በክትትል ሂደት ላይ ነው፡፡

- የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ በሀገር ውስጥ እና ኢንተርናሽናል ጨረታ ወጥቶ በሂደት ላይ ነው፡፡ ታህሣሥ 18 እና ጥር 14/2017 ዓ.ም ጨረታው ተከፍቶ ግዢው የሚከናወን ይሆናል (ክንውን 100%)፡፡

11.1.2 በጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት በዓለም ባንክ ብድር የተገዙ አዳዲስ የላቦራቶር መሳሪያዎችን እና ከቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የመጡ መሳሪያዎችን በመከታተል ወደ ስራ በማስገባት ሪፖርት ለማቅረብ ታቅዶ

- በጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት የተገዙ 5 የTemperature Indicator/Readout for PRT & TC/ የላቦራቶር መሳሪያዎች እና 21 የላቦራቶር ወንበሮች በመከታተል ወደ ስራ ገብቷል፡፡
- በጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት የተገዙ አዳዲስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን አይነትና ብዛት በስም በመለየት የላቦራቶሪ አሬንጅመንት ተደርጓል
- በዓለም ባንክ የተገዙ ለላቦራቶሪ መሳሪያዎች ገጠማ የሚዉሉ14 ቤንቾች ገጠማ ተጠናቋል፡፡ በዝርዝር መስፈርቱ መሰረት ተገምግሞ ጉድለቶቹ እንዲሟሉ አቅራቢዉ ተጠይቋል፡፡
- የኬሚካል ላቦራቶሪ ግላስ ዌር ከኮተቤ ወደ መገናኛ ግቢ በማጓጓዝ በዝርዝር መስፈርቱ መሰረት ተገምግሞ ጉድለቶቹ እንዲሟሉ ለአቅራቢ ድርጅት ተገልጿል፡፡ ተጨማሪ 7 የብረት 4 የእንጨት ጠረጴዛዎች እና 13 ወንበሮች ገቢ ተደርገዋል፡፡ ለመሳሪያዎች ገጠማ የሚያከናዉኑ ባለሙያዎች እየተጠበቁ ይገኛል (ክንውን 100%)፡፡

**11.2 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** (ክንውን 83%) ፡፡

**11.2.1** የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው ለመፈራረምና ለመመዘን ታቅዶ የ2016 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር አፈጻጸም እና የ2017 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ በአብዛኛው ስራ አስፈፃሚዎች ወርዶ ተፈራርሟል (ክንውን 83%) ፡፡

## 3. ዓበይት ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎኖች

### ጠንካራ ጐኖች

- በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ በ4 ላብራቶሪዎች ማስመዝገብ መቻሉ፡፡
- በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር መቻሉ
- የቴክኒክ ድጋፍ እና የምክር አገልግሎቶች መሰጠቱ፤
- በውስጥ ካሊብሬሽን፣ በተንቀሳቃሽ እና በመስክ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት መቻሉ፤
- የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት መቅረቡ፤

### ደካማ ጐን

- ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት አፈጻጸም፤
- ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት አለመቻሉ
- አገልግሎት አሰጣጡ በዜጎች ቻርተር በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑ መከታተል አለመቻሉ
- ከጥራት መሰረተ ልማት ጋር በመተባበር ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ማካሄድ አለመቻሉ
- በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠና ማግኘት አለመቻሉ
- ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የትብብር ስምምነት ማደስና መፈጸም
- ከጀርመን (PTB) እና ከደቡብ ኮርያ (KRISS) ሥነ-ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነቶችን ማደስ እና ተግባራዊነቱን መከታተል

## 4. በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ተግባራት

- የአዳዲሶቹ ህንጻዎች የውስጥ ስርዓትና ዩቲልቲ ማጠናቀቂያ ስራዎችን መከታተል
- በጥራት መሰረተ ልማት ህንጻዎች ግንባታ ምክንያት የተቋረጡ የዓለም ዓቀፍ እውቅና ወሰኖችን ለማስመለስ በትጋት መስራት፤
- የዓለም ዓቀፍ የእርከን ተዋረድ ሰትስስር ስራዎች በወቅቱ እንዲከናወኑ ክትትል ማድረግ፤
- የንጽጽር ፕሮግራሞች ተሳትፎን ለማሳደግ የሚያስችሉ ክትትሎችን ማጠናከር፤
- አዳዲስ ክልሎችን በህጋዊ ስነልክ ዘርፍ ድጋፎችን ለማድረግ የሚሰሩ ስራዎችን በፍጥነት መከወን፤
- የመሳሪያዎች ግዢና የቅርንጫፍ ላብራቶሮችን የማጠናከር ስራዎች መከታተል።

## 5. የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወር የሰው ኃይል መረጃ ሪፖርት

| ተ.ቁ | የሠራተኞች የት/ደረጃ | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | | | በ6 ወራት ውስጥ አዲስ የተቀጠሩ | | | በ6 ወራት ውስጥ አዲስ የለቀቁ | | | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | 1ኛ-12ኛ | 14 | 21 | 35 | - | - | - | 1 | 1 | 3 | 13 | 19 | 32 |
| 2 | TVT (Level) | 5 | 13 | 18 | - | - | - | - | - | - | 5 | 13 | 18 |
| 3 | ዲኘሎማ (10+3) | 9 | 5 | 14 | - | - | - | - | - | - | 9 | 5 | 14 |
| 4 | ቢ.ኤ/ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 76 | 45 | 121 | | - | - | 3 | 2 | 5 | 76 | 43 | 119 |
| 5 | ኤም.ኤ/ኤም.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 25 | 7 | 32 | - | - | - | - | - | - | 25 | 7 | 32 |
| 6 | ፒ.ኤች.ዲ | 1 | - | 1 | - | - | - | - | - | - | 1 | - | 1 |
| ድምር | | 130 | 91 | 221 | - | - | - | - | - | 8 | 129 | 87 | 216 |

| 6. | የ2017 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የፋይናንስ አፈጻጸም | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ | በ2017 በጀት ዓመት የ 6 ወራት የፋይናንስ ዕቅድ | በ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት ወጪ | | የ6 ወራት የፋይናንስ አፈፃፀም ከ6 ወራት ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር |
| | ከመንግስት | | ከመንግስት | ከውጭ እርዳታ | |
| መደበኛ በጀት | | | | | |
| ፕሮግራም 01 | 86,782,800.00 | 31,199,583.27 | 21,949,307.46 | | 70.35 |
| ኘሮግራም 02 | 15,808,335.00 | 11,519,855.37 | 11,299,798.03 | | 98.08 |
| ፕሮግራም 03 | 13,323,600.00 | 11,533,942.84 | 6,754,590.97 | | 58.56 |
| ፕሮግራም 04 | 14,806,303.00 | 12,354,881.58 | 3,169,064.27 | | 25.65 |
| ንዑስ ድምር | 130,721,038.00 | 66,608,263.06 | 43,172,760.73 | | 64.81 |
| ካፒታል በጀት | 70,518,250.00 | - | 0 | | 0 |
| ድምር | 201,239,288 | 66,608,263.06 | 43,172,760.73 | | 64.8 |

## 7. ማጠቃለያ

የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ መሰረት ያደረገው የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ  እና የ3 ዓመት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ (2017-2018) መሰረት በማድረግ ፣የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማካተት እና የኢንስቲትዩቱን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚ ፣ ስጋትን በመተንተን እንዲሁም 11 ስትራቴጂያዊ ግቦችን በማካተት በዋና ዋና እና ዝርዝር ተግባራት የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ተከልሶ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን ከዓለም አቀፍ ሥነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ስርዓትን ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ 126(ወ=129, ሴ=87) ሠራተኞችን ይዞ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2017 በጀት ዓመት በስድስት ወራት የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ከማሳደግ አንጻር ለ 13474 የመለኪያ መሳሪያዎች የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ለ135 ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በሥነ-ልክ ዘርፍ በአሜሪካው ፋርማኮፒያ የባዮሜዲካል መሐንዲሶች በCold chain equipment and General Metrology ፣የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትየት ባለሙያዎች፣ የሙቀትና ወበቅ ሥነ-ልክ ምርምር ዴስክ ተመራማሪዎች እንዲሁም ከሸገር ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ አመራሮችና ቡድን መሪዎች፣ ከአዲስ አበባ ተግባረእድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የ legal metrology ስልጠና በ volume, mass, balance ,dimensional and pressure የተግባር ስልጠና በህጋዊ ስነልክ ፣በሚዛን መስፈሪያ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ዙሪያ ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ከጤና ሚኒስትር ጋር በተደረገ የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት በኤሌክትሮኒክ ቦርድ ጥገና ላይ የጽንሰ ሀሳብ እና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በሥነልክ ዘርፍ ለኢትዮጵያ ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራዝ ፣ ለኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ፣ለኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ፣ለምርምር ስልጠና ማእከል የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለሚያቋቁሙ ተቋማት በጥያቄያቸው መሰረት 100% የቴክኒክ፣ የድጋፍ እና የምክር   አገልግሎቶች ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ  የስራ ክፍሉ ባለሙያዎች በአዲስ አበባ በሚገኙ 9 የጤና ተቋማት በመሄድ ኢንስቲትዩታችን በህክምና መሳሪያዎች ዘርፍ የቴክኒክ እገዛ እንደሚያደርግ  እና ለሚቀርቡ የምክር ጥያቄዎች  የምክር   አገልግሎቶች እንደሚሰጥ ገለጻ ተደርጓል፡፡

ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት አንጻር በውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ በሙቀት እና በኤሌክትሪካል ካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ጊዜያቸዉ የደረሰ ማነጻጸሪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል፡፡

የአለካክ ወሰኖችን ከማሳደግ አንጻር በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ላይ የስልጠና ቢጋራ (TOR) ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ነገር ግን እስከ አሁን በተለያዩ ምክንያት ስልጠና ባይሰጥም በcentrifuge calibration ላይ በራስ ባለሙያ በማንበብ ስልጠና በመስጠት ስራ ተጀምሯል። እንዲሁም በፎቶሜትሪ /photometer/ የአለካክ መስክ ላይ በኢንስቲትዩቱ አማካሪ በዶ/ር ፍራንዝ አማካኝነት ስልጠና በመዉሰድ የካሊብሬሽን አገልግሎት ተጀምሯል፡፡

ማህበራዊ አገልግሎት በተመለከተ ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት 8,856 ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ደመዎዛቸው አነስተኛ ለሆኑ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ከሠራተኛ ክበብና ከሌሎች ሠራተኞች በማስተባበር ለአዲስ ዓመት የዱቄትና ዘይት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለመቅዶንያ አረጋውያን መረጃ 93,750 ብር ማዕድ የማጋራት ስራ ተሰርቷል::

በስድስት ወራት ውስጥ ብር 4,965,050 የአገልግሎት ክፍያዎች ተሰብስቦ ለገ/ሚ ገቢ የተደረገ ሲሆን የስድስት ወራት የተግባር አፈጻጸም 84.5% ሲሆን የበጀት አፈጻጸሙ 64.4% ሆኗል፡፡

## 8. የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸ ም % |
| ግብ 1 | የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ | | | | | |
| 1.2 | የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.2.1 | ለ8500 ዓለም ዓቀፍ ትስስር የጠበቀ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | 24854 | 34000 | 17000 | 13474 | 79 |
| 1.3 | የጥገና (የቴክኒክ አገልግሎት ) መስጠት አገልግሎቶች | | | | | |
| 1.3.1 | ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና(የቴክኒክ) አገልግሎት መስጠት | 252 | 350 | 155 | 135 | 79 |
| 1.4 | **የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት (ክብደት 4.5)** | | | | | |
| 1.4.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች ስልጠና መስጠት | 6 | 8 | 4 | 5 | 125 |
| 1.5 | **የቴክኒክ ድጋፍ እና ምክር አገልግሎቶች መስጠት(ክብደት 6)** | | | | | |
| 1.5.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለግል ባለሃብት፣ ለህጋዊ ሥነ-ልክ፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለሚያቋቁሙ የግል ባለሃብት ወ.ዘ.ጥያቄ ለሚያቀርቡ 100% የቴክኒክ እና የምክር አገልግሎቶች መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6 | **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት (ክብደት 1.5)** | | | | | |
| 1.6.1 | ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ ለሚጠይቁ ደንበኞች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት | 100 | 100 | 100 | 0 | 0 |
| ግብ 2 | ተደራሽነትን ማሳደግ | | | | | |
| 2.2 | **የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ሳቢና ኢንተራክቲቭ እንዲሆን ማድረግ** | | | | | |
| 2.2.1 | ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ማዘጋጀት፣መጫንና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ | 4 | 4 | 6 | 20 | 100 |
| 2.2.2 | ለዌብሳይት ተጠቃሚዎች ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ | 4 | 4 | 2 | 2 | 100 |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸ ም % |
| 2.3 | **የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን መስጠት** | | | | | |
| 2.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ጋር በመተባበር ግንዛቤ ለማስጨበጫ ፕሮግራሞች ማካሄድ | 2 | 3 | 1 | 0 | 0 |
| **ግብ 3** | **የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ** | | | | | |
| 3.1 | **የበጀት አጠቃቀምን መከታተል** | | | | | |
| 3.1.1 | የፀደቀውን በጀት በእቅዱ መሰረት 100% መጠቀም | 94 | 100 | 100 | 64.4 | 64.4 |
| 3.2 | **የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ** | | | | | |
| 3.2.1 | የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | 13 ሚሊዮን | 15 ሚሊዮን | 5,700,000 | 4,965,050.15 | 87 |
| 3.3 | **የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** | | | | | |
| 3.3.1 | የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት | 5 | 6 | 4 | 4 | 100 |
| **ግብ 5** | **አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** | | | | | |
| 5.1 | **ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማስራጨት (ክብደት )** | | | | | |
| 5.1.2 | በውስጥ ካሊብሬሽን፣ በተንቀሳቃሽ እና በመስክ የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ (Reference Standard) መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስራጨት:: | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 5.3 | **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት** (ክንውን 58%)፡፡ | | | | | |
| 5.3.1 | በሁለት ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች የግዝፈት እና የሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች በኢትዮጵያ የአክሪዲቴሽን አገልግሎት አክሪዲቴሽን ማግኘት | 0 | 1 | 1 | 0.6 | 60 |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸ ም % |
| 5.3.2 | በቀጣይ ዓለም አቀፍ ዕውቅና የሚጠየቅባቸው (የጨረራ፣ የፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እና የኬሚካል) የአለካክ መስኮች የልኬት ወሰን መለየት | 0 | 3 | 3 | 1.5 | 50 |
| 5.4 | በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB) ማስመዝገብ (ክብደት 4) | | | | | |
| 5.4.2 | በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ያለ በይዘት ለማስመዝገብ ክትትል ማድረግ | 0 | 1 | 1 | 4 | 100 |
| 5.5 | **ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ** | | | | | |
| 5.5.1 | AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት | 1 | 2 | 1 | 1 | 100 |
| 5.6 | **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | |
| 5.6.1. | የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት አደረጃጀት ለዉጥ ምክንያት በISO 17025:2017 የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት Quality manual ለመከለስ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 6 | **የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** | | | | | |
| 6.1 | **የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ (ክብደት 6)** | | | | | |
| 6.1.2 | በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠናዎችን ማግኘት፣የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማጠናቀቅ የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር | 0 | 4 | 2 | 1 | 50 |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸ ም % |
| 6.1.4 | በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር | 0 | 2 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 7 | **የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል** | | | | | |
| 7.1 | **የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** (ክብደት 1) | | | | | |
| 7.1.2 | የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና አገልግሎትን የኦንላይን አገልግሎት በከፊል ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል | 0 | 1 | 1 | 0.5 | 50 |
| 7.1.3 | የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን የኦንላይን አገልግሎት ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 0 | 4 | 2 | 1.9 | 95 |
| 7.2 | **ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ (ክብደት 1.5)** | | | | | |
| 7.2.1 | በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ማስጠበቅ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.2.2 | ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ | 100 | 100 | 100 | 0 | 0 |
| 7.3 | **የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም** | | | | | |
| 7.3.1 | በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ማጠናቀቅ | 1 | 2 | 1 | 0.6 | 65 |
| 7.4 | **የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ** | | | | | |
| 7.4.1 | በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ | 1 | 1 | 1 | 0.8 | 80 |
| ግብ 8 | **ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** | | | | | |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸ ም % |
| 8.2. | **ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | |
| 8.2.1 | ከጀርመን (PTB) እና ከደቡብ ኮርያ (KRISS) ሥነ-ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነቶችን ማደስ እና ተግባራዊነቱን መከታተል | 1 | 2 | 1 | 0 | 0 |
| 8.3 | **ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት (ክብደት 0.5)** | | | | | |
| 8.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | 4 | 4 | 2 | 2 | 100 |
| ግብ 9 | **የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ** | | | | | |
| 9.1 | **የሰው ሀብት ልማት ማልማት** | | | | | |
| 9.1.1 | ሠራተኞች ስልጠና መስጠት | 151 | 125 | 60 | 135 | 100 |
| 9.1.2 | ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት | 2 | 3 | 3 | 1 | 33.33 |
| 9.2 | **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር** | | | | | |
| 9.2.1 | ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ | 19495 | 19560 | 9780 | 8856 | 90.55 |
| 9.3 | **የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ (ክብደት 2.5)** | | | | | |
| 9.3.1 | በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የስነምግባር መመሪያ ማጠናቀቅ፣ | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 9.3.2 | በተቋሙ በህግ ሀብት ማስመዝገብ የሚገባቸው ሰራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ መከታተል፣ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ግብ10. | **የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል** | | | | | |
| 10.1 | **የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ (ክብደት 1)** | | | | | |
| 10.1.1 | የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ | 4 | 4 | 2 | 2 | 100 |

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2016 መነሻ | የ2017 ዕቅድ ኢላማ | የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸ ም % |
| 10.2. | ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት | | | | | |
| 10.2.1 | የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ማድረግ (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ እና እድሳት) | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10.3 | የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ (ክብደት 4) | | | | | |
| 10.3.1 | ለነባር ሲስተሞችን (ኢፍሚስ፤ ኢጂፒ፤ ኢስሚስ፤ ኢሜል፤ዌብሳይት) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | 4 | 4 | 2 | 2 | 100 |
| 10.3.2 | የኢንስቲትዩቱነን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | 4 | 4 | 2 | 2 | 100 |
| 10.4 | **የተቋማዊ ለውጥ የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት (ክብደት 3.5)** | | | | | |
| 10.4.2 | የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት እንዲፈቱ ለሚመለከተው በማቅረብና እርምጃ ማስወሰድ | 1 | 1 | 1 | 2 | 100 |
| 11 | **የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** | | | | | |
| 11.1 | **ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ (ክብደት 2)** | | | | | |
| 11.1.1 | ከመንግስት በጀት የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም መከታተል | 0 | 4 | 2 | 1.59 | 100 |
| 11.1.2 | በዓለም ባንክ ብድር የተገዙ አዳዲስ የላቦራቶር መሳሪያዎችን እና ከቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት የመጡ መሳሪያዎችን በመከታተል ወደ ስራ በማስገባት ሪፖርት ማቅረብ | 0 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 11.2 | **የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** | | | | | |
| 11.2.1 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረምና መመዘን | 1 | 1 | 1 | 0.83 | 83 |